**መመሪያ ቁጥር፡ 1037/2017**

**<u>የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የትምህርት ቤቶች ፈቃድ አሰጣጥ እና ዕድሳት መመሪያ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 1037/2017</u>**

በ2016 ዓ.ም. የወጣውን የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የትምህርት ቤቶች ፈቃድ አሰጣጥ እና ዕድሳት መመሪያ ቁጥር 992/2016 ለአፈፃፀም የተሻለ ግልፅነት እንዲኖረው ለማስቻል መመሪያውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡

የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር የፌደራል አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2013 አንቀፅ 19(4) እና አንቀፅ 34(1)(ለ) እና (ሸ) መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

**<u>2. አጭር ርዕስ</u>**

ይህ መመሪያ **"የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የትምህርት ቤቶች ፈቃድ አሰጣጥ እና ዕድሳት መመሪያ (ማሻሻያ) ቁጥር 1037/2017"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **<u>ማሻሻያ</u>**

የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የትምህርት ቤት ፈቃድ አሰጣጥ እና ዕድሳት መመሪያ ቁጥር 992/2016 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

1/ ከመመሪያው አንቀፅ 2(17) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 2(18) ተጨምሯል፡

> ''18. የትምህርት ክፍያ ጭማሪ ማለት፣ አንድ ትምህርት ቤት በቀደመው ዓመት በሚያስከፍለው የትምህርት ክፍያ ላይ አዲስ ክፍያ መጨመር ማለት ሲሆን፣ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ለተመሳሳይ ትምህርት ወይም የክፍል ደረጃ የሚከፈሉ የተለያዩ ክፍያዎችን በማስተካከል ለተመሳሳይ ትምህርት ወጥ ወይም አንድ አይነት ክፍያ እንዲኖር የማድረግን የክፍያ ማጣጣም አሰራርን (Harmonization of school fees) አይጨምርም። ''

2) የመመሪያው አንቀፅ 2(18) እና 2(19) እንደ ቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገው አንቀፅ 2(19) እና አንቀፅ 2(20) ሆነዋል።

3. **መመሪያው የሚፀናበት ቀን፡**

1)ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር እና በፍትሕ ሚኒስቴር ድረ ገፅ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

2) በዚህ መመሪያ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው ቢኖርም፣ የትምህርት ክፍያ ማጣጣምን በሚመለከት በክርክር ላይ ያሉ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ፡፡

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)

የትምህርት ሚኒስትር